አባይ

ይነበብ ይግለጡ

የአባይ ወንዝ ግድብ ታላቅ ሀገራዊ ሕልምና ተስፋ ነው፡፡ የዛሬው ብቻ ሳይሆን የመጪውም ትውልድ ታላቅ ሀገራዊ የልማትና የእድገት ራእይ በተግባር የሚገለጥበት ግዙፍ ግድብ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ 58 በመቶ ደርሶአል፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መሐንዲሶቹም እኛ፤ አናጢዎቹም እኛ፤ ግምበኞቹም እኛ ሁነን፤ በታላቅ ሀገራዊና ሕዝባዊ መነሳሳት ከድህነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ በራሳችን አቅም፣ ያለአንዳች የውጭ እርዳታና እገዛ እንሰራዋለን ነበር ያሉት፡፡ እንዳሉትም እውን ሆነ፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከጅምሩ ጀምሮ ብዙ ያከራከረ፣ ብዙ የተባለለት፣ በሀገርም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ትኩረትን የሳበና ያነታርክ የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያ በራስዋና በልጆችዋ አቅም የጀመረችውን የግድቡን ግንባታ ቃሏን ጠብቃ ወደ ፍጻሜው ለማድረስ በትጋት እየሠራች ትገኛለች፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታው አስፈላጊው ደረጃ ላይ ሲደርስም የውሀ መሙላትና ማከማቸቱ ተግባር በየደረጃው ይቀጥላል፡፡ የአባይ ወንዝ የእኛው ቢሆንም ድንበር ተሻጋሪና የአለም አቀፍ ወሰኖችን የሚያቋርጥ በመሆኑ ኢትዮጵያ አቅም አግኝታ ግድቡን ከሰራች የውሀው ፍሰት ይቀንሳል በሚል፤ በተለይ ግብጽ በየዘመኑ  ያላሴረችብን ሴራ፣ ያልቆፈረችልን ጉድጓድ የለም፡፡

ኢትዮጵያ በሰላም የምታምንና ሰላም አክባሪ ሀገር ነች፡፡ የአባይ ውሀ ተፈጥሮ በጋራ እንድንጠቀምበት ተፈጥሮ የሰጠን፣ የተጋሪዎቹም የጋራ ሀብት ስለሆነ በጋራና በሰላም ልንጠቀምበት እንችላለን በሚል ዛሬም በእምነትዋ ጸንታ ቀጥላለች፡፡ ይህ እውነትና እምነት የማይዋጥላቸው አካላት በተለይ ግብጽ እንደጥንቱ ሴራና ደባዋ ሁሉ ዛሬም ከጀርባ ሁና ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን በሁሉም መስክ በመርዳትና በማገዝ የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት ለማደፍረስ ከዲፕሎማሲ ጨዋታው ጀርባ ሌላ ሰፊ ቁማር እንደምትጫወት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ በትክክል ያውቁታል፡፡

ባለፈው አመት በሀገራችን ውስጥ ከተከሰተው ግጭት፣ የሰላም እጦትና አለመረጋጋት ጀርባ በተለይ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች በነበረው እንቅስቃሴ የግብጽና የኤርትራ መንግሰት ስውር እጆች በስፋት እንደነበሩበት ይታወቃል፡፡ ዘንድሮ በእሬቻ በአል ለተፈጠረው ትርምስና እጅግ አሳዛኝ የዜጎች ሕይወት መቀጠፍ ከጀርባ ያቀናበሩት ኦነግ፣ ጀዋር መሀመድና የግብጽ ደህንነት ለመሆናቸው በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡

ኢትዮጵያ  የራሴን የተፈጥሮ ሀብት፣ የአባይን ወንዝ ውሀ በመጠቀም የማልማት መሰረታዊ መብት አለኝ፤ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ከውሀው ማግኘት ያለባቸውን ድርሻ ያገኛሉ፡፡ የግድቡ መሰራት በውሀው መጠን ላይ የሚያደርሰው ችግር የለም፤ ግድቡ የአካባቢውንም፤ ሀገሮች ተጠቃሚ ያደርጋል የሚለውን አቋሟን በተደጋጋሚ ገልጻለች፡፡

ዛሬም የአባይ ውሀ ሁላችንም በጋራ እንድንጠቀምበት ተፈጥሮ የሰጠችን በረከት ስለሆነ  ለውዝግብ መነሻ ሊሆን አይገባም በሚለው እምነትዋ ጸንታለች፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ተገቢና ትክክለኛ አቋም ነው፡፡ ግብጾች የእነሱ ባልሆነው የተፈጥሮ ሀብት ምንጩ ኢትዮጵያ መሆንዋን እያወቁ የአባይ ውሀ ታሪካዊ ባለቤቶች ነን ሲሉ እውነቱን የሚያውቀው የአለም ሕዝብ እየሳቀባቸው መሆኑን ለመረዳት ያልቻሉ ናቸው፡፡ ግብጾች ኢትዮጵያ አንድ ቀን አቅም አግኝታ በአባይ ውሀ ላይ ግድብ ትሰራለች የሚለው ከጥንት ጀምሮ የነበራቸው ፍርሀት በኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ ዘመናት ታላላቅ ወንጀሎችን እንዲፈጽሙ አድርጎአቸዋል፡፡ ኢትዮጵያን ለመውጋትና ለማዳከም ከሚደረጉት ጦርነቶች ጀርባ ጥንትም ዘንድሮም ግብጾች ነበሩ፡፡ ዛሬም እንደዛው፡፡ ትርፉ ወርደትና ውድቀት እየሆነባቸው መጨረሻቸው ሁሉ ክሽፈት ሆነ እንጂ።

ግብጾች ለዘመናት በአባይ ውሀ ሲጠቀሙ፣ የተለያዩ ግድቦች ሲሰሩ፣ ልማቶችን ሲያካሂዱ፣ ሰው ሰራሽ ሀይቆችን ሲፈጥሩ፣ ታላላቅ የሙዝና ብርቱካን እርሻዎችን በማልማት ለአለም አቀፍ ገበያ እያቀረቡ ብሔራዊ ገቢያቸውን ሲያሳድጉ ወዘተ ባለቤትዋ ኢትዮጵያ በራስዋ የአባይ ውሀ ግድብ እንዳትሰራ አለም አቀፍ ጫና እስከመፍጠር ተራምደው ነበር፡፡

ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ለሚሰራ ማንኛወም ግድብ አለም አቀፍ ብድር እንዳታገኝ ታላላቆቹን መንግስታትና የብድር ተቋሞቻቸውን ጭምር በመጠቀም ግብጽ ስታስከለክል ኖራለች፡፡ ዛሬ ግዜው ባልተጠበቀ ሁኔታ ተለውጧል፡፡ ኢትዮጵያ የአባይን ወንዝ ተጠቅማ ግድብ ለመስራት የማንንም የውጭ ሊጋሽም ሆነ አለም አቀፍ ድርጅት ብድር አልጠየቀችም፡፡ በራስዋ ህዝብ ተማምና በራስዋ አቅም ነው ለመስራት የተነሳቸው፡፡

ግብፅም ሆነች ሌሎቹ ድሀ ሀገር ስለሆነች ግድብ ለመስራት የሚያስችል አቅም የላትም በሚል በመጀመሪያ ላይ ተሳልቀው ነበር፡፡ እነሱ ጠግበው ሲያድሩ የአባይ ውሀ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ለበርካታ አመታት በድርቅና ቸነፈር እየተመታች እርዳታ ጠያቂና ተመጽዋች ሀገር ሁና የኖረችበትን አስከፊ የትላንት ታሪክ እያስታወሱ በምን ተአምር ነው በከፋ ድህንት ውስጥ የኖረች፤ የራስዋን ሕዝብ መግባ ለማኖር እንኳን ያልቻለች ሀገር እንዴት አድርጋ አባይን ያህል ነገር ትገድባለች? በማለትም ተሳልቀው ነበር፡፡ ራእያችንን ሕልምም አድርገው የቆጠሩም አልጠፉም፡፡ ሕልሙ እውን ሲሆን፣ መጀመሩን ሲያረጋግጡ ጦርነት እናውጃለን፤ እንመታለን ወዘተ በማለት ፈጥነው አካኪ ዘራፍ ማለቱን ተያያዙት፡፡

ጥንትም ጉራና ጉንደት ላይ ዘልቀው ጦርነት የከፈቱት ግብጾች የኢትዮጵያ መሬት መቀበሪያቸው ሁኖ በውርደት በሽንፈት ተመለሱ፡፡ በኤርትራ በኩል ከጀርባ ሁነው ተደጋጋሚ ጦርነት ከፈቱ፡፡ በመጡበት ሁኔታ ወርደትና ሽንፈታቸውን ተከናንበው ተመለሱ፡፡ በሶማሊያ በኩል ግብጾች ከጀርባ ሁነው አሰልቺና ረዥም ጦርነት ከፈቱ፡፡ ግብጽ ከሶማሊያው መሪ ዚያድ ባሬ ውድቀትም በኋላ የነበሩትን የተለያዩ የጦር መሪዎች በመርዳትና በማስታጠቅ ኢትዮጵያን እንዲወጉ አደረገች፡፡ በዚህም ግንባር ተሸነፈች፡፡

ግብጽ አነግን ኦብነግንና ሌሎችንም መርዳቱን እስከዛሬም ቀጠለች፡፡በሽንፈትና በውድቀት ምእራፍ ቀጠሉ እንጂ አንዳቸውም ለስኬት አልበቁም፡፡ወደፊትም አይሳካላቸውም፡፡ግብጽ  የኤርትራውን መሪ በመጠቀም ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን ሴራዋን ዛሬም ማሴሩን ቀጥላለች፡ ፡ መቼም አይሳካላትም፡፡የግብጽ መሪዎች በዚህ አለምና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ በሚያውቀው ሴራቸው ትዝብት ላይ ወድቀዋል፡፡

እኛ ብቻ እንኑር ሌላው ይጥፋ በሚለው ስግብግብና ሰብአዊነት በጎደለው አቋማቸው ይታወቃሉ፡፡ኢትዮጵያ የአባይ ውሀ ለሁላችንም ይበቃል ተደማምጠንና ተከባብረን ብንጠቀምበት ለሁላችንም ይበጃል ነው ያለችው፡፡ግብጾች ደግሞ እኛ ብቻ የፈለግነውን የመጠቀም መብት አለን ባይ ናቸው፡፡ከየት የመጣ ማን የሰጣቸው መብት ነው ሲባል በቅኝ ግዛት ዘመን እንግሊዝ ባለቤትዋ ኢትዮጵያ በሌለችበት ለግብጽና ለሱዳን የአባይን ውሀ መጠንና ድርሻ ማከፋፈልዋን በዋቢነት ይጠቅሳሉ፡፡

ያንን የባርነት ዘመንዋን የሞኝ ዘፈን ይዛ ስታላዝን የኖረቸው ግብጽ ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ስር ያልወደቀች በቅኝ ግዛት ዘመን ውልና ስምምነት የማትገዛ የማትቀበል ሀገር መሆንዋን አምና መቀበል ተስኖአት ኖራለች፡፡የአባይ ውሀ 85 በመቶ ,ምንጩ ኢትዮጵያ መሆንዋን አለም ያውቃል፡፡በጋራ መጠቀም እንችላለን፡፡ይሄ ዘመኑ የሚፈቅደው በሳል ግንዛቤ ነው፡፡

ዛሬ ላይ ግንባታው እንደተጀመረ ሰሞንና የመጀመሪያዎቹ አመታት አይነት የነበረው ጩሀትና እሪታ በብዙ መጠን ቀንሶአል፡፡ኢትዮጵያ የጀመረችው  የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ በምንም መንገድ ሊቆምና ሊገታ እንደማይችል የተገነዘቡበት ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡ የግድቡ ግንበታ ስራ ከነበረበት ተነስቶ 58 በመቶ መድረሱ ታላቅ ሀገራዊ ስኬትና ድል ነው፡፡ተጠናክሮም በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡ይህ ግድብ ስራው ሲጠናቀቅ በአለማችን ሰባተኛው በአፍሪካ ደግሞ የመጀመሪያው ትልቅና ግዙፉ ግድብ ይሆናል፡፡

የግድቡ ግንባታ በስራው ላይ በተሰማሩት ኢትዮጵያውያኖች ያለአንዳች እረፍት ለሊት ጨለማውን ብርሀን በማልበስ የቀኑ የበረሀ አየርና ንዳድ ሳይበግራቸው ሀገራዊና ሕዝባዊ አደራቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡የሕዳሴው ግድብ ግንባታ በስኬት መገባደድ ለሀገራችን ዳግም ውልደትና ታላቅ ትንሳኤ ነው፡፡ኢትዮጵያ በሰላምና በመነጋገር ተቀራርቦ ልዩነቶችን በመፍታት በጋራ ተጠቃሚነት በመልካም ጉርብትናና ወዳጅነት መርህ የምታምን ሀገር ነች፡፡

የግብጹ አስዋን ግድብ ግብፅን ወደ840ሺ ሔክታር መሬት ዓመቱን በሙሉ በመስኖ እንድታለማ አስችሏታል፡፡ዋና ዋና የግብጻዊያኑ ምርት ጥጥ፣ ሸንኮራ አገዳ ሩዝና ስንዴ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ይኸ ሁሉ ተዳምሮ ግብጽ ምዕራብ እና ምስራቅ አፍሪካን በ1964-1965 እና በ1975 1979 ያጠቃው ድርቅ አልደረሰባትም፡፡ግድብ ድርቅን መቀልበሻ አንድ ትልቅ መፍትሄና ቁልፍ ጉዳይም ነው፡፡በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ግድብን መገንባት ግዙፍ ጥቅም ያለው ሲሆን ለመስኖ ስራም ወሳኝና አስፈላጊ ስለሆነ የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት ያበቃናል፡፡እኛም የተለየ ትኩረት ልንሰጠውም ይገባናል፡፡

የተፈጥሮ አቅም ውስን በመሆኑ ሌሎችም መጋራት ያለባቸው ኃብት መሆኑን መቀበል ተገቢ ነው፡፡እድገት ወሰን አለው፡፡የሕዝቡም ቁጥር ያለገደብ ማደግ የለበትም፡፡ ኢኮኖሚው ሊሸከመው የማይችል ያልተመጠነና የተንቦረቀቀ የሕዝብ እድገት ያልተገመተና ያልታሰበ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ውድቀት ያመጣል፡፡የበለጸጉ ሀገሮች በቤተሰብ ምጣኔ በመመራታቸው ነው ኢኮኖሚያቸውም ያደገው፡፡ችግሮችንም በማስወገድ መራመድ የቻሉት፡፡ይህንን እያደረጉም ዛሬም ችግሮች በስፋት አሉባቸው፡፡

ኢትዮጵያ አቅም አግኝታ በዓባይ ወንዝ ላይ የባለቤትነት ጥያቄ ወይንም የመጠቀም እርምጃ ትወስዳለች ተብሎ አይገመትም ነበር፡፡ይህንን አላማቸውን ለማሳካት ከጥንት ጀምሮ ሀገሪቷ እንድትከፋፈል ሰላም እንድታጣ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር አንድነቷን ለማናጋት በተወጠነው ሴራ ፋታ አግኝታ በዓባይ ላይ ምንም ዓይነት ሥራ እንዳትሠራ ሲያደርጉ መኖራቸው ይታወቃል፡፡የሀገሪትዋ ጠላቶች ደባ ዛሬም በአዲስ ዘዴና መልክ መልኩን ቀይሮ የቀጠለ ሲሆን ሁልግዜም ለዚሁ ሴራቸው የሚያስማሩዋቸው የራሳችንን ዜጎች ዘመን የማይሽረው እውነት ሁኖ ዛሬም ቀጥሎአል፡፡

ማጠቃለያ

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንበታ 58 በመቶ ደርሶአል፡፡በተቀመጠለት አቅጣቻ መሰረት ስራው ሌት ከቀን በተጠናከረ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡የግድቡ እዚህ ደረጃ መድረስ ራሱን ችሎ ታላቅ ሀገራዊ ስኬትና ድል ነው፡፡በተሳካ ሁኔታም ይጠናቀቃል፡፡